16ኛ ዓመት ቁጥር 10
16th Year No. 10

ባሕር ዳር ህዳር 12 ቀን 2004 ዓ.ም
Bahir Dar November 22, 2011

bxþT×eÃ ØÁ‰§êE ÁäK‰sþÃêE ¶pÜBlþK
yx¥‰ B¼¤‰êE KLL MKR b¤T

# ZKr ÞG

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

bx¥‰ B¼¤‰êE KL§êE mNGST MKR b¤T «ÆqEnT ywÈ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ÃNÇ ዋU BR 11.60
Unit price 11.60

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 182/2003 ዓ.ም

የተሻሻለዉን የምክር ቤት አባላት ሥነ-ምግባር፣ የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራር መወሰኛ አዋጅ ለመሻር የወጣ አዋጅ

**Contents**

**Proclamation No.182/ 2011**

**A Proclamation issued to repeal the Revised Council Members' Ethics, Legislative Procedure, Committee Organization and Operation**

## አዋጅ ቁጥር 182/2003 ዓ.ም

**የተሻሻለዉን የምክር ቤት አባላት ሥነ-ምግባር፣ የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራር መወሰኛ አዋጅ ለመሻር የወጣ አዋጅ**

የክልሉ ም/ቤት በሕገ-መንግስቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በተሻለ መልኩ መወጣት የሚያስችለዉን ወጥ የሆነና የተጀመረዉንም ፓርላሜንታዊ ዴሞክራሲ በከፍተኛ ደረጃ ማዳበር የሚያስችል የአሰራር ሥነ-ሥርዓት ያወጣ በመሆኑ፡፡

በዚህ የተነሳም በስራ ላይ ያለዉን የምክር ቤት አባላት ሥነ-ምግባር፣ የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራር መወሰኛ አዋጅ መሻር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፡፡

## Proclamation No.182/2011

**The Revised Council Members' Ethics, Legislative Procedure, Committee Organization and Operation Proclamation Repealing Proclamation**

Whereas, the Regional Council has issued Rules of Procedure which enable discharge its Constitutionally entrusted responsibility in a better way, and transfer the on going parliamentary System building to a highe lever thereof.

Whereas, necessary to repeal the applicable council Members', Ethics, legislative procdure, Committees Organization and operation proclamation therein.



የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት በተሻሻለዉ የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንኡስ አንቀጽ 3/1 በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይህንን አዋጅ አዉጥቷል።

<u>አንቀጽ **1.** አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የተሻሻለዉን የምክር ቤት አባላት ሥነ-ምግባር፣ የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራር መወሰኛ አዋጅ መሻርያ አዋጅ ቁጥር 182 /2003 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

<u>አንቀጽ **2.** ስለመሻር</u>

የሚከተሉት አዋጆች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

1. የተሻሻለዉ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት ሥነ-ምግባር፣ የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 119/1998 ዓ.ም እና
2. የተሻሻለዉ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት ሥነ-ምግባር፣ የሕግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራር መወሰኛ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 126/1998 ዓ.ም።

<u>አንቀጽ **3.** አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ-ሕግ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ባህር ዳር

ህዳር 12 ቀን 2004 ዓ.ም

አያሌዉ ጎበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት

Now, therefore; the Council of the Amhara National Region, in accordance with the Powers vested with it under Sub-Article 3/1 of Article 49 of the Revised Constitution of the Region, hereby proclaims as follows:

<u>**Article 1. Short Title**</u>

This Proclamation may be cited as"the Revised Council members' Ethics, Legislative Procedure, Committee Organization and Operation Proclamation Repealing Proclamation No.182 /2011"

<u>**Article 2. Repeal**</u>

The following proclamations are hereby repealed by this proclamation:

1. The Revised Amhara National Regional Council Members Ethics', Legislative Procedure, Committees Organization and Operation Determination Proclamation No. 119/ 2005, and
2. The Revised Amhara National Regional Council Members 'Ethics, Legislative Procedure, Committees Organization and Operation Determination Proclamation Amendment Proclamation No. 126/2006.

**ደንብ ቁጥር 9/1997**

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አባላትን ሥነ ምግባር፣ ለመደንገግ የወጣ ደንብ

ለብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤትና ለተዋረድ ምክር ቤቶች በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት የተሰጣቸው ሥልጣን ከፍተኛ እና ባለብዙ ፈርጅ እንደመሆኑ መጠን ይህንን ከባድ ኃላፊነት በሚገባ መወጣትና ዴሞክራሲያዊ አሠራርን በይበልጥ ማጐልበት የሚታመንበት በመሆኑ፣

ከዚህም የተነሣ የተሻሻለውን ሕገ-መንግስትና መራጩ ሕዝብ በምክር ቤት አባላት ላይ አመኔታ ባጣ ጊዜ የሚወስዱ እርምጃዎችን አስመልክቶ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 23/1990 ዓ.ም ድንጋጌዎች በተሟላ መንገድ የሚያስተገብር ወጥ የሥነ-ምግባር ደንብ አውጥቶ በሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል ቤት ተሻሻሎ በወጣው የክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/16 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

**1.** አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት የሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 9/1997 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2.** ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ቁጥር፦

1."ምክር ቤት" ማለት የብሔራዊ ክልሉ ም/ቤት ሲሆን የብሔረሰብ ዞን፣የወረዳና የቀበሌ ም/ቤቶችን ይጨምራል።

2."የሕዝብ ተወካይ" ማለት የም/ቤቱ አባል ነው።

3. "አዋጅ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልል፣ የብሔረሰብ ዞን፣የወረዳና የቀበሌ ም/ቤቶች አባላት ላይ መራጩ ሕዝብ አመኔታ በሚያጣባቸው ጊዜ ስለሚወስድ እርምጃ የወጣው አዋጅ ቁጥር 23/1990 ዓ.ም ነው።

**3.** የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የሕዝብ ተወካይ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ክፍል ሁለት

የሥነ-ምግባር መርሆዎች

**4.** መሠረታዊ መርሆዎች

ማንኛውም የሕዝብ ተወካይ፦

1. ለመረጠው ሕዝብ እና ለሕገመንግስቱ ታማኝ መሆን አለበት።
2. የብሔራዊ ክልሉንና የፌዴራሉን ሕግጋተ-መንግሥታት ጨምሮ ሌሎች ሕጐችን ማክበርና ማስከበር አለበት።
3. ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ኃላፊነቱን የሚወጣው የክልሉን ሕዝብ ጥቅም በማስቀደም ዓላማ ላይ ተመስርቶ ይሆናል።

**Article 3. Effective Date**

This proclamation shall come in to force as of its publication on the Zikre- Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar,

This 22th day of November,2011

Ayalew Gobezie

President of the Amhara National Region

## Proclamation No. 9/2004

## A Regulation Issued to Provide for the Ethics of the Amhara National Region Council Members

WHEREAS, as the Regional Council and hierarchal Councils are vested with supreme and multi-dimensional power by the Revised Constitution of the Region, and it is hence believed to properly discharge such a huge responsibility and to better promote democratic practice;

WHEREAS, it has, as a result, become necessary to issue and implement an ethical regulation for the holistic execution of the Revised Constitution and stipulations of Proclamation No.23/1997, issued regarding measures taken against members of the Council when the electorates lose confidence thereon;

Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it under Article 49 sub- Article 3/16, issues the following Regulation.

**PART ONE**

**General**

1. **Short Title**

4. የሕግ የበላይነት እና መልካም አስተዳደርን የማጐልበት አስተዋፅኦ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡
5. የአደባባይም ሆነ የግል ኑሮውን በመልካም ሥነምግባር በመምራት የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ ማስጠበቅ አለበት፡:

**5.** <u>ለሕሊና ተገዢነት</u>

የሕዝብ ተወካይ ከማናቸውም ዓይነት ተፅዕኖ ነፃ በሆነ ሕሊና ለምክር ቤቱ በቀረቡ አጀንዳዎች ላይ መምከር፣አስተያየቶችን መስጠትና ውሣኔዎችን ማሣለፍ አለበት፡፡

**6.** <u>ተጠያቂነት</u>

የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 48/4/እና /5/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም የሕዝብ ተወካይ ለሚሰጣቸው ውሣኔዎችና ለሚያከናውናቸው ሌሎች ተግባራት ሕዝባዊ ተጠያቂነት አለበት፡፡

**7.** <u>ኃላፊነትን ስለመቀበል</u>

የሕዝብ ተወካይ ለምክር ቤቱ ሥራዎች ክንዋኔ በማናቸውም ደረጃ እንዲያገለግል ሲመረጥ በሙሉ ፈቃደኝነት ኃላፊነቱን የመቀበል ዝግጁነት ይጠበቅበታል፡፡

**8.** <u>አደራን በሚገባ ስለመወጣት</u>

የሕዝብ ተወካይ፡-

1. እውቀቱንና የሥራ ልምዱን አሟጦ በመጠቀም የተጣለበትን ሕገ-መንግሥታዊና ሕዝባዊ አደራ በሚገባ መወጣት አለበት፡፡

2. አደራውን ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት መሣሪያ ማድረግ የለበትም፡፡

**9.** <u>አርአያ ስለመሆን</u>

ማንኛውም የሕዝብ ተወካይ፡-

1. ሥራውን በሚያከናውንበት ወይም በማሕበረሰቡ ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ ግንባር ቀደምና ምሣሌ በመሆን የሚጠበቅበትን ከፍ ያለ የአርአያነት ጠባይ በማሣየት በዚህ ደንብ ውስጥ የተመለከቱትን መርሆዎች ማጐልበትና በተግባር እንዲተረጐሙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

2. ሐላፊነት የሚሰማው፣ የተሻለ ለውጥን የሚደግፍ፣የምክር ቤቱን መልካም ስም የሚጠብቅና የአሠራር ባህል እንዲዳብር፣ መተማመን ሥር እንዲሰድና ፀንቶ እንዲቆይ የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡

**10.** <u>የዜጐችን መብትና ጥቅም ስለማስከበር</u>

በምክር ቤቱ እንደአግባቡ የሚፀድቅ ሕጐችና የሚተላለ Õ <u>ውሣኔዎች</u> ፡-

1. በሕገመንግሥቱ የተደነገጉትን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች የማይቃረኑ፣
2. መላው የክልሉ ሕዝብ በክልሉ ሀብት ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የሚታቀፍበትን አግባብ የሚያመቻቹ መሆናቸውን ማረጋገጥ ከሕዝብ ተወካይ የሚጠበቅ ግዴታ ነው፡፡

**11.** <u>አድልዎ ስላለመፈፀም</u>

የሕዝብ ተወካይ በዘር፣በቀለም፣ በፆታ፣ በብሔር/ ብሔረሰብ፣

This Regulation may be cited as "The Amhara National Region Council Members Ethical Regulation No.9/2004."

## 2. <u>Definitions</u>

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1. "Council" means the Council of the National Region and includes the Councils of the Nationality Zone, Woreda and Kebele.
2. "People's Representative" means a member the Council.
3. "Proclamation" means proclamation No.23/1997 issued to provide the measure to be taken against the members of Councils of the Region, Nationality Zone, Woreda and Kebele in the Amhara National Regional State when the electorates lose their confidence upon them.

## 3. <u>Scope of Application</u>

This Regulation shall apply to people's representatives found at all levels

# <u>PART TWO</u>
# <u>Ethical principles</u>

### 4. <u>Fundamental Principles</u>

Any people's representative shall :

1. be loyal to the electorate and the Constitution.
2. respect and cause the observance of Constitutions of the National Region And of the Federal including other laws.
3. discharge his responsibilities based on the objective to serve the interest of the people of the Region.
4. be expected to make contribution to promote the prevalence of the rule of law and good governance.
5. Cause respect and grace of the Council to be observed by leading his public as well private life with good conduct.

## 5. <u>Obedience to conscience</u>

A people's representative shall deliberate, comment and pass decisions on agendas presented to the Council with conscience free

በቋንቋ፣በሃይማኖት፣በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ልዩነት ሳያደርግ አድልዎ በሌለበት ሁኔታ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት።

**12.** <u>ግልጽነትና ሐቀኝነት</u>

ማንኛውም የሕዝብ ተወካይ፡-

1. የሕዝብን ጉዳይ አስመልክቶ በተለያዩ መድረኮች በሚወያይበት ጊዜ ግልጽ መሆን አለበት።
2. እውነት አለመሆናቸውን እያወቀ የሐሰት ማስረጃዎችን ወይም ያልተጣሩ ጉዳዮችን ወደ ም/ቤት መደረክ ማቅረበና መዋሸት የለበትም።

**13.** <u>ሚስጢር ስለመጠበቅ</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ 12 እና በክልሉ ሕገመንግሥት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 5 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቱ በዝግ ስብሰባ የወሰናቸውንና የክልሉንና የሕዝቡን ጥቅምና ደህንነት ከማስከበር ጋር ተያያዥነት እንዳላቸው ተገልፆ ለም/ቤቱ ውይይት የቀረቡ መረጃዎችን በሚስጢርነት መጠበቅ አለበት።

**14.** <u>የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ስለማክበር</u>

የሕዝብ ተወካይ ለምክር ቤቱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት የመገዛት ግዴታ  አለበት።

**15.** <u>አቅምን ስለማሳደግ</u>

ማንኛውም የሕዝብ ተወካይ በሕዝቡ የተጣለበትን አደራ በብቃት ለመወጣት ያስችለው ዘንድ የሚያገኘውን ትርፍ ጊዜ አቅሙን ሊያሳድጉ በሚችሉ ተግባራት ላይ የማዋል ዝንባሌን ማዳበር አለበት።

**16.** <u>የሕዝብ አቤቱታን ስለማስተናገድ</u>

የሕዝብ ተወካይ ከዜጐች የሚቀርብለትን የሕዝብ አቤቱታ በከበሬታ ተቀብሎ ማስተናገድ፣ ተገቢውን እልባት በአፋጣኝ ለማስገኘትም ጉዳዩን በትጋት መከታተል ይኖርበታል።

**17.** <u>ሀብትና ንብረትን ስለማስመዝገብ</u>

አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ማንኛውም የሕዝብ ተወካይ ሀብትና ንብረቱን የማስመዝገብ ግዴታ  ይኖርበታል።

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>ስለዲሲኘሊን እርምጃ</u>

**18.** <u>መሠረቱ</u>

የዲሲኘሊን እርምጃ የሚወሰደው በአዋጁና በዚህ ደንብ የተደነገጉትን የሥነ-ምግባር መርሆዎችን በማስከበር ዓላማ ላይ ተመሥርቶ ብቻ ይሆናል።

**19.** <u>የዲስኘሊን እርምጃ ስለመውሰድ</u>

1. ማንኛውም የሕዝብ ተወካይ የሚጠበቅበትን ሥነ-ምግባር

of any influence.

**6. <u>Accountability</u>**

Without prejudice to the provisions of Article 48/4/ and /5/ of the Constitution of the National Region,any people’s representative shall have public accountability with respect to decisions he renders and other duties he discharges.

**7. <u>Taking on Responsibility</u>**

A people’s representative shall be expected to take on responsibilities with complete willingness when he is elected to serve the undertaking of the oouncil(not editing error) at any level.

**8. <u>Discharging trustship Appropriately</u>**

A people’s representative:

1. Shall discharge properly the constitutional and public trust lied upon him by making use of his all Knowledge and work experience
2. shall not instrumentally use the trust lied upon him so as to gain inappropriate benefits or to favor same another person.

**9. <u>Being Exemplary</u>**

Any people’s representative shall:

1. Promote and cause the practical implementation of principles indicated in this regulation by showing the higher exemplary behavior, which is to be expected of him being vanguard and exemplary, while carrying out his task or inhabiting in the society.
2. have a sense of responsibility, uphold better change, maintain good reputation of the Council and cause trustship to be deep rooted and remain sustained thereon.

**10. <u>Enforcing the respect for rights and interest of nationals</u>**

It is duty of a people’s representative that laws and decisions which the Council accordingly approved and pass:

1. Shall not contradict with the

አጓድሎ ከተገኘ የዲሲኘሊን እርምጃ ይወስድበታል።

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሥነ-ምግባር ጉድለት ተጠያቂ የሚሆን የሕዝብ ተወካይ ራሱን የመከላከል መብት ይኖረዋል።

**20.** የሥነ -ምግባር ጉድለት ጉዳዮችን ስለማጣራት

ማናቸውም የሥነ-ምግባር ጉድለት ጉዳይ ምክር ቤቱ በሚያቋቁመው ኮሚቴ አማካኘነት ይጣራል።

**21.** <u>ኮሚቴውን ስለማቋቋም</u>

1. የሥነ-ምግባር ጉድለት ጉዳዮች አጣሪ ኮሚቴ ምክር ቤቱ ከአባላቱ መካከል አውጣጥቶ የሚያቋቁመው ይሆናል።
2. ኮሚቴው ከአምስት እስከ ሰባት አባላት ይኖሩታል።
3. የኮሚቴው ሰብሳቢ የሚሆነው አባል በምክር ቤቱ ይሰየማል።
4. የኮሚቴው አባላት አገልግሎት የሚሰጡበት ጊዜ ኮሚቴውን ያቋቋመው የወቅቱ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል።

**22.** <u>ስለኮሚቴው የስብሰባና የአሠራር ሥነ-ሥርዓት</u>

የሥነምግባር ጉድለት ጉዳዮች ለኮሚቴው የሚመሩት በምክር ቤቱ አፈጉባዔ ወይም እንደሁኔታው በምክር ቤቱ አማካኘነት ይሆናል።

2. ከኮሚቴው አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዐተ-ጉባዔ ይሆናል።

3. ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ በድምፅ ብልጫ የተደገፈ ይሆናል፣ ድምፅ እኩል ለእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ኮሚቴው የራሱን የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**23.** <u>ውሣኔ ስለመስጠትና ስለማስፈፀም</u>

1. ምክር ቤቱ የተፈጸመውን የሥነ-ምግባር ጥፋት እንደሁኔታው ቀላል ወይም ከባድ መሆኑን አጣሪ ኮሚቴው አጥንቶ በሚያቀርብለት የውሣኔ ሃሣብ ላይ ተወያይቶ ውሣኔ ሃሣብ ላይ ተወያይቶ ውሣኔ ይሰጣል።
2. ምክር ቤቱ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።
3. ትክክለኛ ውሣኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ም/ቤቱ ተጨማሪ የማጣራት ሥራ እንዲካሄድ ጉዳዩን መልሶ ለኮሚቴው ሊመራው ይችላል።
4. በም/ቤቱ ውሣኔ መሠረት የሚወስደውን

fundamental rights and freedoms enshrined in the Constitution.

2. Shall be conducive for circumstances in which all peoples of the Region are embraced to equitably benefit from resources of the Region.

**11.** **<u>Impartiality</u>**

A people’s representative shall discharge his responsibilities regardless of discrimination on grounds of race, color, sex, nation/nationalities, language,religion, political outlook or on other statues.

**12.** **<u>Transparency and honesty</u>**

Any people,s representative

**16.<u>Entertaining public Complaints</u>**

Any people’s representative shall entertain with respect public complaints submitted to him,and actively follow up the case to urgently result in an appropriate solution thereto.

**13.** **<u>Getting assets and properties Registered</u>**

Any people’s representative shall have an obligation to get his assets and properties registered pursuant to appropriate law.

**14.**

**15.**

**16.**

**17.**

የዲሲፕሊን እርምጃ የየደረጃው አፈ-ጉባኤው ያስፈጽማል፡፡

**24.** <u>ስለዲሲፕሊን ቅጣት አይነቶችና አፈጻጸማቸው</u>

1. በሥነ-ምግባር ጉድለት ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ የሕዝብ ተወካይ ላይ የሚጣሉ የዲሲፕሊን ቅጣቶች አይነትና ተፈፃሚ የሚደረጉበት አግባብ በአዋጁ አንቀጽ 6/3/እና /4/በተመለከተው መሠረት ም/ቤቱ የሚወስደው የዲሲፕሊን እርምጃ እንደሁኔታው ከሚከተሉት አንዱ ይሆናል፡-

ሀ.የቃል ማስጠንቀቂያ ወይም ተግሳጽ፣
ለ. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣
ሐ. ከምክር ቤት አባልነቱ በሕግ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ ታግዶ መቆየት፣

መ. በከባድ ወይም በተደጋጋሚ ጥፋት ሳቢያ በም/ቤቱ ውሣኔና በሕግ መሠረት ከሕዝብ ተወካይነት መወገድ፡፡

2. በሕዝብ ተወካዩ ላይ የተወሰደው እርምጃ ስንብትን ወይም ስረዛን የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ ውሣኔውን መራጩ ሕዝብ እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡

**25.** <u>ከምክር ቤት አባልነት የመወገድ ውጤት</u>

አንድ የሕዝብ ተወካይ በሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት ከምክር ቤት አባልነቱ ሲወገድ የአዋጁ አንቀጽ 7/1/ በሚደነግገው መሠረት በኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አማካኝነት ተፈጻሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**26.** <u>የዲሲፕሊን ክስ የሚቀርብበት ጊዜ</u>

1. በዚህ ደንብ የተቀፃፈው የሥነ-ምግባር ድንጋጌ የተጣሰ እንደሆነ የጥፋቱ መፈጸም ከታወቀበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ የዲሲፕሊን እርምጃ ጥያቄ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፣
2. የዲሲፕሊን ቅጣት የወንጀል ወይም የፍታብሔር ተጠያቂነትን አያስቀርም፡፡

**27.** <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች የክልሉ ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**28.** <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

**1.** ይህ ደንብ ከመውጣት በፊት ሲሰራበት በቆየው የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት አባላት መተዳደሪያና ውስጣዊ

## <u>PART THREE</u>

## <u>Disciplinary Measures</u>

**18.<u>principle</u>**

A disciplinary measure shall only be taken based on the objective of observance to ethical principles stipulated in the proclamation and the Regulation hereof .

**19.<u>Taking a Disciplinary Measures</u>**

1. A disciplinary measure shall be taken against any people’s representative where he is found in breach of the ethics expected of him.
2. Without prejudice to the stipulation of Article I of this Article, a people’s representative who is held liable for breach of ethics shall have the right to defend himself.

**20. <u>Inquiring Cases of Ethical Breaches</u>**

A committee to be established by the Council Shall inquire any case of ethical breach.

**21.<u>Establishment of the Committee</u>**

1. Inquiring committee for cases of ethical breach shall be established among members drawn from the Council.
2. The committee shall have five to seven members.

አሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ ደንብ ቁጥር 5/1994 ዓ.ም ውስጥ ከአንቀጽ 21 እስከ 23 ያሉት ድንጋጌዎች ተሽረው በዚህ ደንብ ተተክተዋል።

**2.** ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**29.** <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕር ዳር

ሕዳር 20 ቀን 1997 ዓ.ም

የሴፍ ረታ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ፕሬዚዳንት

3.The chairperson of the committee shall be designated by the Council.

4.The term of office of members of the committee shall be the term of office of the Council that has established the committee.

22. **<u>Meeting and Working procedure of the Committee</u>**

1. Ethical breaches shall be referred to the Committee by the Speaker of the Council as the case may be.
2. There shall be a quorum where half of members of the committee present at its meeting
3. The decision that the committee recommends shall be supported by a majotity vote, incase of a tie, however, the chairperson shall have a casting Vote.

4.Without prejudice to the stipulations of this Article, the committee may draw up its own working procedure determination directive.

23.**<u>Decision and Execution</u>**

1. The Council shall discuss and pass decision on the recommendation, which the inquiry committee verifies and submits to it whether the committed ethical breach is simple or grave, as the case may be.

2. The decision of the Council shall be final.

3. The Council may refer the case back to the committee for further inquiry where it deems necessary to make a correct decision.

4. Speaker of each level shall execute the disciplinary measure taken in accordance with the decision of the Council.

**24.<u>Types of Disciplinary Measures and their Execution</u>**

1. The disciplinary measure which the

Council takes with regard to the types and execution

Circumstances of disciplinary measures imposed against a peopl's representative who is pleaded guilty of ethical breaches,pursuant to Article 6/3/ and /4/ of the proclamation, shall,as the case may be, be one of the following.

A. Oral warning or reprimand;
B. Written warning ;
C. Suspension of him from membership of the Council for a specified duration of time pursuant to law;
D. Dismissal from his constituency by the decision of the Council and pursuant to law due to grave or repeated offences;

2.Where the measure taken against a people's representative is found to be concerned with dismissal or cancellation, the electorate shall be made to have Knowledge of the decision.

**25. Effect of Dismissal from Membership of the Council**

1. Where a people's representative is dismissed from membership of the Council due to ethical breaches,the decision shall be executed by the Ethiopian National Electorate Board pursuant to the provision of Article 7/1/of the proclamation.

## PART FOUR
## Miscellaneous provisions

**26.Time of Disciplinary Charge**

1.Where the ethical rule stated in this Regulation is violated and unless a question of disciplinary measure is brought against such a case within one year from the date of the commission of the offence is known,the case shall be barred by period of limitation.

2. A disciplinary measure shall not prohibit criminal or civil liability.

27.**Power to Issue Directives**

The Speaker of the Regional Council may issue directives necessary for the execution of this Regulation.

**28.Repealed and Inapplicable Laws**

1.The provisions stated from Article 21 to 23 in the Revised Amhara National Region Council Members Administration and Internal Working procedure Determination Regulation No.5/20002,which has been in effect prior to the Issuance of this Regulation, are hereby deleted and replaced with this Regulation.

2.Any regulation, directive or customary practice Inconsistent with this Regulation shall be inapplicable on matters provided in this Regulation.

**29. Effective Date**

This Regulation shall come into force as of the date of its publication in the *Zikre Hig Gazetta* of the Regional State

Done at Bahir Dar,

This 29 day of Nov.2004

Yosef Retta
President of the Amhara National Region